# የወያኔ (ኢሕአዴግ) ተቀዋሚ ሀይሎች (ፓርቲዎች) ትላንት፣ ዛሬና ወደፊትስ?

ምጸአተ-እስራኤል ከተሰኘው መጸሀፍ ውስጥ ''....እንኳን የሚኖሩበት፣ የሚሞቱለት ሀገር ያላቸው የታደሉ ናቸው።...'' የሚል ሀረግ አለበት። አዎ... እስራኤላዊያን ሀገር ባልነበራቸው ወቅት፤ የሚኖሩበት አይደለም ''ሀገሬ'' የሚሉት ኑሮ'ቸው፤ የሚጠይቀውን ሁሉ መሰዋእትነት ለመክፈል ይመኙ ነበር። ተመኝተው ግን አልቀሩም፤ ምኞታቸውን ተገበሩት። 'የሚሞቱለት ሀገር ብቻ አይደለም የሚኖሩበትም ሀገር' ባለቤት ሆኑ።

ወደ እኛ ስንመጣ በተለይም በወያኔ ዘመን ተኮትኩተን ያደግን ትውልዶች የምንኖርበትም ሆነ የምንሞትላት ሀገር እያጣን ነው። እርግጥ ነው በሀገሩ ላይ በሰላም መኖር የብዙሀኑ የሰው ልጅ ፍላጎትና ምኞት ነው። ታዲያ የሰው ልጅ መብቱ ሲደፈር፤ ማንነቱነና ነጻነቱን ለማስከበር ሲል ለሀገሩ ይሞታል። ሀገር ሁሉም ነገር ናትና። የሰው ልጅ ያለሀገሩ ምን ቁሳዊ ዓለሙ ቢሟላለት ክብረ-ቢስና የመንፈስ ደሀ ነው። የምኞት ሁሉ ቁንጮዎች የሆነው ደስተኛ የመሆን ፍላጎት ቅዥት እንጅ አውን አይሆንም። ለዚህም ነው እስራኤላዊያን ''....እንኳን የሚኖሩበት፣ የሚሞቱለት ሀገር ያላቸው የታደሉ ናቸው።...'' ለማለት የተገደዱት እንጅ ለመሞት ፈልገው አልነበረም።

የ'ኛ የኢትዮጵያዊያን የአሁን ሁኔታችንና ስራችን ካለፉት ዘመናት ሁሉ ውስብስብ፣ ግራ የሚያጋባ፣ የሚሳዝንና እንደ እግር እሳት የሚያገበግብ ነው። ሁለት ምክንያቶች ብቻ ልጥቀስ፤.......

**1ኛ/ በዘርና በቋንቋ ከፋፈለው ፣ የሚለያዮንና ሀገራችን እያፈራረሱ፣ ክቡር መሬታችን ለታሪካዊ ጥላቶቻችና ለባዕዳን የሚሸጡብንና ከወገኖቻችን ለያይተው የባህር-በር አሳጥተው፣ ደካማና ለማኝ አድርገው ፣ ከቻሉ እንደ ጨው አሟሟተው ሊያጠፉን የሚፈልጉት ''በመበረ-መንግሥትነት'' ላይ የተቀመጡት የገዛ ወገኖቻችንና በኢትዮጵያና በአትዮያዊነት ስም የሚንቀሳቀሱት ፍጹማዊ አምባገነን መሆናቸው።**

**2ኛ/ ወያኔ/ሻአቢያዎች ለእኩይ አላማቸው፤ በሀገሪቱ ጥላቶች ተደራጅተውም ሆነ 'ራሳቸውን አደራጅተው ኢትዮጵያንና ኢትጵያዊነትን በተለያየ መንገድ የምንኖርባት አይደለም የምንሞትላት ሀገር ለማሳጣት ዓመታት ሙሉ በጽናት ሲታገሉ፤ በተቃረኒው ለሰናይ ምግባር ኢትዮጵያንና ለኢትዮጵያዊያን ለማትረፈና፣ ለተተኪው ትውልድ ለማስረከብ የሚካሄድ እስካአሁን ድረስ ተጨባጭና ውጤታማ ትግል አለመኖሩ ሌላው አስገራሚና አሳዛኝ ምክንያት ነው ።**

***''...........አየሽ እናታለም! ... .....................***

***የአ'ች እኮ ... ውድቀትሽ ብቻ አይደለም የሚያሳዝነው***

***ከውድቀትሽ ለማትረፍ፣ የሚደረግ ጥረት አለመኖሩ ነው***

***ዓለምን አስደምሞ፣ እጅግ አድርጎ የሚያስገርመው።''*** */ ''አትጥሪኝ አልመጣም...'' ከተሰኘው ግጥም የተውሰደ። /*

ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ባለቤት አ'ታ ወይም ለችግሯ መድህኒት እንደጠፋ ሁሉ ቁምጥና እንደያዘው አካል እየተቆራረጠችና እያለቀች ነው። ልጆቿ በሀገር ውስጥም ሆነ በስደት ምጻተኞችና ተቀበዝባዦች ሆነናል። ገዥዎቻችን ኢትጵያንና ኢትዮጵያውነትን የማጥፋት አላማቸውን እየፈጸሙና እያስፈጸሙ ነው። አላማቸውም ስለሆነ፡ ***''ለምን ትከፋፍሉናችሁ?፣ ለምን ትዘርፉናላችሁ? ለምን መሬታችን ለባዕዳን ትሸጣላችሁ?፣ ለምን ትውልድን ታጠፋላችሁ?፣ ወዘተ....''*** **ብሎ መጠየቁ ፍይዳ የለውም። የሞቱለት፣ የገደሉብት፣ ያስገድሉበት፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነታቸውን የከዱበትና ያስከዱበት ''ክቡር'' አላማቸው ነውና።** በተግባርም ደጋግመው አሳይተውናል። በ'ርግጥ 'እያየ ለታወረ፣ እየስማ ለደነቆረ፣ እየተራብ ለጠገበ፣ እየታረዘ ለለበሰ፣ እየሞተ ለሚኖር....ወዘተ ኢቲቪን አዘጋጅተዋል።

የገዥዎቻችን አለቃ አቶ መለስ ዜናዊ፤ ህዝብን የመበታተኑን፣ ትውልድን ወኔና አላማ-ቢስ ወይም ስደትኛ የማድረጉ፣ ሀገርን የማፍረሱንና ለባዕዳን ሽጦ የመጨረሱን፣ በአጠቃላይ የጥላቶቻችንን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ሳይፈጽሙ በድንገተኛ ሞት ሲለዩ፤ ''አ'ማ'ላኪዎቻቸው'' ወያኔዎችና ደጋፊዎቻችው አቶ መለስ ያላጠናቀቁትን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን

የማጥፋት እኩይ ምግባር ''እኛ እናጠናቅቀዋለን!'' በማለት እንደተለመደው በህዝብ ህይወትና በሀገር ላይ በመቀለድ ከፍ ዝቅ በማለት ላይ ናቸው።

በአቶ መለስ ሞት ወቅትና ከቀብርም በኋላ ገዥዎቻችን የሚያሳዮት ተውኔት፤ ህዝብና ሀገር ማለት እነሱ የፈጠሩን፣ እንደፈለጉ የሚጫወቱብን ክብርና ስብዕና የሌለን አሻንጉሊቶች አድርገው እንድሚያዩን አረጋግጠውልና።

ነገር ግን **"የእናቴ መቀነት አደናቅፎኝ ነው።"** የሚለውን የጦጢትን ምክንያት ትተን፤ እውነት እንነጋገር ከተባለ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያኖች ዛሬ ከደረስንበት ውርደትና ውድቀት ከወያኔዎችና ከሻአቢያዎችም ሆነ ከውጭ ጥላቶቻችን ይልቅ በተቃራኒው ጎራ የቆመው (እኛ) ተጠያቂ ነው። "የጥላትህ ጥንካሬ የአንተ ድክመት ነው።" የሚለውን ማጤን ይገባል። ትግሉ ደግሞ ለፍትህና ለእኩልነት ከሚደረግ ወይም አምባገነን ከማሰውገድ ባላይ ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥልና ትውልድ የማትረፍ ትግል ።

***....እናት-አራስ መሆን እወቂበትና***

***መሀጸ ንሸን ባርኪው ዛሬም እንደገና፤***

***"ሙቼ እየተነሳው፣ ልሙት እንደገና***

***ለሀገሬ አንድ ሞት አይብቃኝምና...."***

***የሚል ታደርሻለሽ ዛሬም ቀን አለና።*** - - - -

ስለዚህም የዛሬው ትኩረታችን በወያኔ ተቃዋሚ ሀይሎች(ፓርቲዎች) ላይ በአጭሩ መመልከት ይሆናል።

## የተቃዋሚ ሀይሎች አሰላለፍና እንታገልለታለን የሚሉት አላማ

### 1ኛ / "ለተወለዱበት ጎሳ ወይም መንደር የሚታገሉ"፤

እነዚህ ሁሉም ማለት ይቻላል የወያኔ ቅኝቶች ናቸው። ወያኔ ካሰመረው መስመር አይወጡም። ምክንያቱም ለመጡብት ጎሳ ወይም መንደር ነጻነትና እኩልነት የሚታገሉ ቢሆን ኑሮ፤ የህዝቡ ኑሮው በተሻሻለና መብቱ በተከበረለት ነበር። ተቃዋሚዎች እንዲባሉ "ደጋፊወቻችን ታሰሩብን።" ሲሉም ይሰማሉ። አንዳንዴም "ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር ሕብረት ፈጠርን፣ የሕብረቱ መሪ 'እኔ ነኝ...እኛ ነን።" ሲሉ ይሰማና፤ ገና የተፈራረሙንበት ቀለም ሳይደርቅ "ፈረሰ" ይሉናል ወይም ድምጻቸው ይጠፋል። ወያኔ የተለመደውን የማጭበርበሪያ ምርጫ ሲጠራ አብረው ያጫፍራሉ። የተወሰኑ "ወንበሮች" ከተፈቀደላቸውም "ሸንጎ" ገብተው "ውጡ በቃችሁ" እስኪባሉ ድረስ ተውኔቱን ያዳምቃሉ። ታዲያ እነዚህ ተቃዋሚዎች በሚገርም ሁኔታ የሚመሩበትም ሆነ የሚተዳደሩበት ግልጽ የሆነ መርሀ-ግብር እንኳን የላቸውም። አመራር አከላት ያላቸው አይመስልም። ከሀያ ዓመት በፊት የምናያቸው "ሊቀመናብርት" አሁንም እነ'ሱ ናቸው። ብዙ ማለት ይቻላል። አላማቸው ግን ግልጽ ነው፤ በወገን ስም እየነገዱ ከወያኔ የምትተርፈውን ፍርፋሪና የሰምቶ አዳሪነት ስልጣን ይዞ እንድ ካሮት ወደታች እያደጉ ማገልገል ነው። እያገለገሉም እስካሁን ድረስ ዘልቀዋል።

## 2ኛ/ "ለዲሞክራሲ፣ ለሀገሪቱና ለህዝቧ ልዕልና የሚታገሉ"፤

"ለዲሞክራሲ፣ ለሀገሪቱና ለህዝቧ ልዕልና የሚታገሉ"፤ በ'ርግጥም በተቃዋሚነት ተደራጅተው መረሀ-ግብር ነድፈው በተውሰነ ደረጃም ቢሆን ታግለዋል። ይሁን እንጂ ከያዙቱ አላማና ካላቸው የህዝብ ድጋፍ አንጻር ሲታይ፤ ወያኔን አስወግደው ኢትዮጵያን የዲሞክራሲ ሀገርና ኢትዮጵያን የኢትዮጵያዊያን ማድረግ በቻሉ ነበር። ነገር ግን ከሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪና ምግባር ውጭ የሆነውን ወያኔን ለማወቅ ባለመቻላቸው፤ ከአምባገነኖች ምንጋጋ ልንላቀቅ ቀርቶ፤ በባሰ ደረጃ ገዥዎቻቸን ሀገሪቱ ራሷንና ውድ ልጆቿ ለዓለም ዲታዎችና ለታሪካዊ ጥላቶቻችን በጨረታ ቸበቸቡን። አሁንም ችብቸባው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ሁሌም የሚነሰው 1997ቱ ነው። ይሁን እንጅ በምጨረሻዋ ሰዓት የትግሉ መሪዎች "ሳይቀናጁ የተቀናጁ" ስለነበሩና ወያኔ እነሱ ከሚያውቁት በበለጠ እነሱን ያውቃቸው ነበርና፤ የብዙ ወገኖቻችን ህይወት ቀጥፎ፣ ብዙዎችንም ለስድትና ለእስር ዳርጎ፣ ለገዥዎቻችን የልብ ልብ ሰ'ቶ ተጠናቀቀ። "የሰላም ትግል" ብዙዎቹን ተስፋ አስቆረጣቸው።

በአሁኑ ወቅት ያሉት የሀገር ቤት ተቃዋሚዎች "መሰብሰቢያ አዳራሽ ተከለከልን፣ ደጋፊዎቻችን ታሰሩብን፣ ወዘተ" ከሚል የተለመደ ወሬ-መሰል ተቃውሞ በቀር፤ ሰላማዊ ትግል የሚጠይቀውን ሁሉ መሰዋአትነት ለመክፈል ተዘጋጅተው፤ ህዝብን አደራጅተውና መሪ ሆነው በተግባር ለውጥ ሊያመጣ የሚችል እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አይታዩም።

## 3ኛ/ "የባህር ማዶ የወያኔ ተቃውሚዎች"፤

የባህር ማዶ የወያኔ ተቃዋሚዎች ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ከሚታገሉት ጀምሮ፣ የኤርትራን መገንጠል እስከ የማይቀበሉትና በገዥው ላይ ጦርነት ያወጁ ሁሉ ያሉበት ሲሆን፤ ከተመሰረቱ የኔን ትወልድ ዕድሜ የሚያስከነዱ ስምና ዝና ለማትረፍ የተሰለፉትን ሁሉ ይጨምራል።

እንዲያውም የኢንተርኔት ድህረ-ገጽን ለሚከታተል በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ የማምጣቱም ሆነ ሀገሪቱን ለመገነጣጠል የሚደረገው ትግል በተለይም በዋሽንግተን፣ በለንደንና በአምስተርዳም ከተሞች ላይ ያለ ይመስላል።

ሁሉም ባህር ማዶ ያሉ የወያኔ ተቃዋሚዎች የሚናገሩተና የሚጽፉት፤ ግን በተግባር የማያሳዩት ነገር ቢኖር "ትግሉ መካሄድ ያለበት በሀገር ውስጥ ነው። የትግሉ ባለቤት ህዝብ ነው።" የሚል ነው። ነገረ ግን ህዝብ ካላደራጁትና ለሚጠይቀው መሰዋአትነት መሪና አር'ያ የሚሆነው ድርጅት ወይም አመራር ሳይኖር እንዴት አድርጎ ነው እንደ ወያኔ ያለ ጭራቃዊ ገዥ ማስወገድ የሚችለው? (እንዲያውም የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያዩ ግዚያት ሆ! በሎ በመውጣት የወያኔ ጥይት በልቶታል። ግን መሪና አደራጅ ስላልነበረውና ስላ'ጣ ሳይሳካለት ቀርቷል። የ1997ቱ ማስታወሱ በቂ ነው።) ተብለወ ሲጠየቁ ደግሞ ማጣፊያው ያጥራቸዋል ወይም "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" አይነት መልስ ይሰጣሉ። ይህ ብቻ አይደለም፤ ወታደር ሳይኖራቸው ጦርነት ያውጃሉ። እነሱ የፈሩትን መሰዋአትነት የሀገር ቤቱ ህዝብ እንዲያደርግላቸው ጥሪ ያስትላልፋሉ። ለ'ነሱ አስፈላጊ መስሎ ከታያቸው ደግሞ ባህር ማዶ ላይ ሆነው የሽግግር መንግስት ይመሰርታሉ ወይም ወያኔን አብረን እንመስርት ይሉታል። በዚህም አያቆሙም፤... በዓመት እስከ 4 ቢሊወን ዶላር ድራስ እየረጠቡት የሚያገለግላቸውን ወያኔን "ለመጣል እየታገልን ነውና እርዱን፣ የፓለቲካም እውቅና ስጡን፣ ወዘተ....።" እያሉ በየቤተ-መንግስታቸው በር ሻማ እያበሩ ይማጸናሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ "የኢትዮጵያ ድንበር ቀይ ባህር ነው" እያሉ፤ እጅግ በሚያሳፍርና የኢትዮጵያዊያንን ክብርና ስብዕና በማዋረድ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂን "ወያኔን ይውጉልን፣ ይረዱን፣ ወታደሮች አሰልጥኑልን፣ ወዘተ....።" በማለት ደጅ ይጠናሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ "ሀገር ቤት መግባት አንችልም።" እያሉ "የሰላማዊ ትግል" አዋጅ ያውጃሉ።

"ለምን ትግላችሁ ውጤት አያመጣም? ወያኔዎች እኮ በኢትዮጵያ ህዝብ(ለሆዱ ካደረው ውጭ)የተጠሉና ድጋፍ የሌላቸው ናቸው።" ተብለው ሲጠየቁ "እየሰራን ነው፣ ገብታችሁ ሞክሩት...ትግላችን የምትተቹ ወያኔ ናችሁ.... ወዘተ" ከማለት ውጭ በተቆርቋሪነት አስተያየት ለሚሰጥ እንኳን በዞዎቹ በጎ አመለካከት የላቸውም። በ'ጠቃላይ "ግራ ገብቷቸው ግራ የሚያጋቡ" ናቸው ብል ማጋነን አይሆንም። ይህን የምለው እድሜ ልክ የወያኔ መቀለጃ ከመሆን፤ ራስን መርምሮ እውነትኛውን የትግል መስመር መያዙ አማራጭ የሌለው አማራጭ በመሆኑ ነው።

እውነታው የባህር ማዶው ትግል የሀገር ቤቱን ትግል ያግዛል። እንደ ኢሳት ያሉ መገናኛ አውትሮችና የኢንተረኔት መገናኛዎች ህዝቡ የበልጠ ግንዛቤ እንዲኖረውና የተለያዩ ሀሳቦች እንድንለዋወጥ ማድረግ ይቻላሉ፤ እያደረጉም ነው። ውሉታቸውን ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ አይረሳም። ሀገር ቤት ያሉትን እውነተኛ የዲሞክራሲ ታጋዮችንና የእስረኛ ቤተሰቦችን በገንዘብም ሆነ በሞራል መርዳትና ማበረታታት ይቻላል። ከዚህ ውጭ ግን ሀገር ቤት ገብቶ የሚጠይቀውን መሰዋአትነት ከምክፍልና ከወያኔ ጋር ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ውጭ የሚደረግ የይሰሙላ ትግል የገዥዎቻችንን እድሜ ሲያራዝም እንጅ ሲያሳጥር አላየንም።

***4ኛ/ "የወያኔ የከፉ ቀን ታጋይ ድርጅቶች (ፓርቲዎች)"፤***

*የወያኔ የከፉ ቀን ታጋይ ድርጅቶች (ፓርቲዎች)፣ በሀገርም ውስጥ ሆነ በባህር ማዶ ተጠናክረው በጽናት የሚሰሩ ናቸው። ብዙዎቹ የድሮ የወያኔ አባል ሲሆኑ፤ በድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን የነበራቸው፣ አድራጊና ፈጣሪም ነበሩ። ከወያኔ "የተለያዮት" አንዳንዶቹ ከስልጣን ፍትጊያና በሀብት ዘረፋው የሚገባንን ያህል አላገኘንም ብለው ሲሆን አንዳንዶቹ ግን ሆን ተብሎ የተባረሩ ናቸው። ለማስመሰል እስር ቤትም ይወረወሩና ከተፈቱ በኋላ አዲስ ግዳጅ ይሰጣቸዋል። ይሁን እንጅ ሁሉም አንድ "ቃል ኪዳን" አላቸው፤ ምንም ምን ቢሆኑ ወያኔን የማገልገል አላማ። እነዚህ ሰዎች በተለያዩ መንግዶች የተደራጁና የሚያደራጁ ሲሆኑ፤ አስፈላጊ ከሆን ጭምብላቸውን አውልቀው (97 ላይ የተከሰትውን እናስታውስ።) በቀጥታ አለያ ግን በተዘዋዋሪ ለወያኔ የሚታገሉ ናቸው። አላማቸውም፤ .....*

***ሀ/ የወያኔ ተቃዋሚ በመምሰል ህዝብን፣ ለዲሞክራሲና ለአንድነት የሚታገሉትን ማሳሳትና ማዘናጋት።***

***ለ/ የራሳቸውን የተቃዋሚ ድርጅት ወይም ፓርቲ በማቋቋምና ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር ህብረት/ አንድነት /መድረክ/ግባር በመፍጠር፣ በሀገሪቱ ውስጥ ጠንካራና ወያኔን የሚያሰጋ ተቃዋሚ እንዳይኖር ማድረግ፤ ካለም እንዲመታ ማድረግ።***

***ሐ/ በተላያዩ የተቃዋሚ ድርጅቶችና ፓርቲዎች ውስጥ ተሰግስገው ለወያኔ መረጃዎችን ማቀበል።***

***መ/ ዋናው ግብ ደግሞ ምናልባት ወያኔ በህዝብ አመፅም ሆነ በተለየ ምክንያት ከስልጣን የሚባረርበት ሁኔታ ቢፈጠር፤ "እኛም ተቃዋሚ ነበርን!" በማለት ስልጣን ኮርቻ ላይ ለመፈናጠጥና የወያኔ ሰዎችንና ጥቅማቸውን በማስከበር በሌላ ዙር ስርዓቱ እንዲቀጥል ማድርግ ነው።***

*በተለይ በአሁኑ ወቅት ትላንት "ትግራይና ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛቶች ናቸው፤ ኢትዮጵያዊ አይደለንም።" በማለት የሙቶ ሺዎችን ወገኖቻችን ህይወት መስዋት አድርገው፤ የባህር-በር አልባ እንዳላደረጉን ሁሉ፣ "ብንፈልግ ጦርነት መፍጠር እንችላለን"፣ወዘተ... በማለት፤ ታሪክና ትውልድ ይቅር የማይለው በደል አንዳልፈጽሙ ሁሉ፤ ዛሬ ደገሞ "የ'ኛ ነጻ አውጭ" ሆነው የመሪነቱን ቦታ ከተቃዋሚ ነን ባዮች ተረክበው ተቆጣጥረውታል። በስውርም ሆነ በአደባባይ ወያኔዎች የሌሉበት የወያኔ ተቃዋሚ ማግኘት ይከብዳል። ግን እነሱማ ምን ያድርጉ? ዘፋኙ እንዴት ነበር ያቀነቀነው?......*

***".....ወሰዱት አሉ የሁመራን መሬት፣***

***የመተማን መሬት.. ያውም የ'ኛን እጣ፣***

***እነሱ ምን ያርጉ ከ'ኛ ሰው ሲታጣ።"***

***ማጠቃለያ፡***

*ወያኔዎች እየተንገዳገዱ ነው። ግን በሚያሳዝን ሁኔታ የሚገፋቸው ስለ'ጡ የሚይዙትንና የሚጨብጡትን አ'ተዋል። ይህ ደግሞ ለማንም አይበጅም። ሰሞኑን 'ለሰፈርተኛ' ወታደሮቻቸው ሹመት ማንበሻበሹ ወደ ወታደራዊ አገዛዘ እያመሩ መሆኑን የሚጠቁም ነው። ይሁን እንጅ የወታደር ጠቅላይ ሚኒስተር ባይሰይሙም፤ አ'ዱን ተነጅ አስቀምጠው እነሱ ከጀርባ ሆነው ለመቀጠል እንድሚሞክሩ አያጠያይቅም። ታዲያ ለእውነተኛ ኢትዮጵያዊያን ተቃዋሚዎች ገ/ማርያም ይግዛ፣ አበበ ይሰየም፣ እመት አዜብ ይገባኛል ትበል፣ አቦይ ያደራጅ-አያደራጅ፣ አባዱላ ይቁም-ይቀመጥ፣ ወዘተ..... ጉዳያቸው ወይም ጉዳያችን መሆን የለበትም። በ'ርግጥ ወያኔዎች ልቦና ገዝተው፣ ህሊናቸውን ፈትሸውና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን እስከአሁን ማጥፋት እንዳልቻሉ አገናዝበው፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ በመጠየቅ፣ሁሉን አቀፍ ለሆነ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር ራሳቸውን ቢያዘጋጁ፤ ለሀገሩ ቅን የሚያስብ ሁሉ ደስታውን ባልቻለው ነበር። ደግሞም ማድረግ ካለባቸው ዛሬ ሳይሆን ትላንት ነበር፤ ትላንትም ባይሆን ዛሬ ነበር። አዎ....ትላንትም ዛሬም አላደረጉትም። ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ባህሪያቸውና አላማቸው አይፈቅድላቸውምና።* ***(ካሰፈለገ አቶ መለስ በሞቱበት ወቅት "አቶ መለስ ዜናዊ ለትውልድና ለሀገራችን ጥለውት ያልፉት እኩይ፣ መራራና አሳዛኝ ሀቆች" በሚል ርእስ የወጣችውን መጣጥፍ ይመልከቱ ። www.zehabesha.com, www.ethiolion.com e.t.c.)***

ስለዚህም ተወደደም ተጠላ ወያኔን ለማስወገድ አስገዳጅ ሀይል መፈጠር አለበት። ከግብጽ፣ ከየመንና ከሌሎቹም ሀገራት ብዙ መማር ይቻለል። እነዚህ ሀገራት ትግላቸውን ያካሄዱት በሀገራቸው ውስጥ በህዝባቸው መሀል መሆኑን የባህር ማዶ ተቃዋሚዎች ከማንኛውም በተለየ ግዜ ዛሬ ልታስቡበትና ወኔ ሊኖራችሁ ይገባል። የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎችም ከፍርሀት ቆፈናችሁ ተላቃችሁ ለህዝብና ለሀገራችሁ ማንነታችሁን የምታሳዮበት ግዜ አሁን ነው። የትግሉ መነሻም ሆነ መድረሻ ለኢትዮጵያናዊያን በኢትዮጵያዊያን እስከ ሆነ ድረስ እንዳለፈው ግዜ "የከከልኝ-ልከክልህ" አይነት ቅንጅት/ካውንስል/ግ'ባር ሳይሆን፤ ለህዝብ ግልጽ የሆነና እውነተኛ ዲሞክራሲ፣ እውነትኛ አንድነትና ህብረት መፈጠር አለበት። ቀኝ ጌታ ዩፍታ ንጉሤ እንዲህ ነበር ያሉት፤....

*"..... አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ*

*ነገራችን ሁሉ የምቧይ ካብ፣ የምቧይ ካብ..."*

ሀገርንና ትውልድን የማትረፍ ጥያቄ፤ ከወሬ፣ ከወረቀትና ከኢተርኔት መፈክር አልፎ፣ እውነቱን በማውጣት፣ ራስን በመፈተሽ፣ ካለፈው በመማርና 'ራስን ለከቡር አላማ ለመሰዋአትነት በማዘጋጀት፤...... **1ኛ/ ተግባር! 2ኛ/ ተግባር! 3ኛ/ ተግባር!**.... ከሁላችንም ይጠበቃል።

---------------------//----------------------------

***ፊልጶስ / መስከረም 2/ 2005***

*ለማንኛውም አስተያየት- e-mail: philiposmw@gmail.com*